# እሮሮ ገድላቸው

ከጠኋት ጀምሮ ፣ በቤተ ክህነት ፤ ያስተማሩት አባ
ቀሚሱን አጥልቆ ፣ ቆብ የተጫነለት ፤ ዘይት የተቀባ
በመንጋ ተመርቶ ፣ ሆይ ሆይታ አሰከረው ፣ በቁም ገደል ገባ
በዓለም ተረታ ፣ ገንዘብ አማለለው ፣ ደለበና ሰባ
የትላንትናው በግ ፣ ፍየል ሆነ ዛሬ ፣ ከንግዲህ አይልም ባ
የት ይደርሳል ያልነው ፣ አድሮ ቃሪያ ሆነ ፣ ለምንም አይረባ ።

አላማው እንዲሰምር ፣ ሲሸረሸር ኖሮ ፤ መስሎ ተለሳልሶ
በጥላቻ በቀል ፣ ዝቅተኛ ስሜት ፣ ተጠምቆ መንኩሶ
አብልታ አጠጥታ ፣ ሰው ያረገችውን ፣ ጎጆዋን አፍርሶ
ቃሊቻ ባለዛር ፣ በል በል የሚል ጂኒ ፣ ውስጡ ገንኖ ነግሶ
ሱሪ ባንገት አውጪ ፣ ሞተሽ ካላየሁሽ ፣ የሚል ጡቷን ነክሶ
በወላጅ እናቱ ፣ ከጠላት ጋር መክሮ ፣ ለሞቷ ደግሶ
ፍርድ እንደተዛባ ፣ የአዞ እንባ ያጎርፋል ፣ በዳይ ሆኖ ለቅሶ ።

ዛሬ በስተርጅና ፣ መቃብር ሊወርዱ ፣ መንገድ የጀመሩ
አንቱ እንዳልተባሉ ፣ በትንሽ ትልቁ ፣ እንዳልተከበሩ
እምነትና ቋንቋን ፣ ለይተው ሳያውቁ ፣ ከንቱ ሲዳክሩ
ጎጥ ጠልፎ ጥሏቸው ፣ ታጥቦ ጭቃ ሆነው ፣ ሲወነካከሩ
አፋቸውን ሞልተው ፣ ፊይሳ አዱኛ ፣ ብለው ሲፎክሩ
ፖለቲካና እምነት ፣ እያደባለቁ ፣ ወደው ቢታወሩ
ለነ አባ እንቶኔ ፣ እኛ አፈርንላቸው ፣ እነሱ ባያፍሩ ።

በኦነግ መሪነት ፣ በመናፍቅ አጀብ ፣ የሞት ሃዋርያ ፤ ሆኖ ለመቀደስ
በአክራሪ እስላሞች ፣ በነ ዋቄ ፈታ ፣ ታጅቦ መኮፈስ
በተዋህዶ ላይ ፣ እንቅልፍ አጥቶ ማደር ፤ የሰው ቤት ለማፍረስ
ትርክት አበጅቶ ፣ እንደተበደለ ፣ በሄዱበት ማልቀስ
በያደባባዩ ፣ ደም የጠማው ሰይጣን ፤ ሄዶ በመቀስቀስ
ሞገዱ ቢያይልም ፣ ኦርቶዶክ ፅኑ ናት ፣ እስከመቼም አትፈርስ ።

የጨለማው ንጉስ ፣ ደቀመዝመዛሙርቶች ፣ ደም ማፍሰስ ህልማቸው
ገዜና ቀን አይተው ፣ አድብተው ገዳዮች ፣ ትላንት ያየናቸው
እነ ጎጥ አምላኩ ፣ ትንንሽ ጭንቅላት ፣ ሰፊ አፍ ያላቸው
ምኞት እንዲሳካ ፣ ተቆርቀቃሪ መምሰል ፣ ስልት አርገው ዘዴያቸው
እሾህ አሜኬላ ፣ የበግ ለምድ ለባሾች ፣ እሮሮ ገድላቸው
ሰላምን አያውቁም ፣ የገሃነም ደጆች ፣ አፈጣጠራቸው ።

ታዛቢው

February 20, 2020